# በመጸዳጃ ቤት በኩል የሚጥሉት ነገር ምንነት ወሳኝ ነው

## 21 በመጸዳጃ ቤት በኩል መጣል የሌለብዎት ነገሮች

- **ሶፍቶች**
- **ፀጉር**
- **የቁስል ፕላስተሮች**
- **ማጽጃዎች ወይም ፀረ-ተባዮች**
- **የጥጥ ኳሶች ወይም የጆሮ መጎርጎሪያዎች**
- **የሲጋራ ጫፎች**
- **ካቴቴሮች**
- **የጥርስ ፍሎስ (ክር)**
- **መጠቅለያዎች**
- **ዳይፐሮች**
- **የሴቶች ንፅህና መጠበቂያ ምርቶች**
- **መድኃኒቶች ወይም ለጤና የሚወሰዱ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮች**
- **የፊት ሕብረ ሕዋሳት**
- **የወረቀት ፎጣዎች**
- **ምርመራ ማካሄጃ ቁርጥራጭ ወረቀቶች**
- **ማስቲካ**
- **ማድረቂያ ወረቀቶች**
- **የድመት ሰገራ**
- **ሃይፖደርሚክ መርፌዎች**
- **የማብሰያ ቅባት**
- **የዓይን ሌንሶች**

### መጸዳጃ ቤት እንጂ ቆሻሻ መጣያ አይደለም።

መጸዳጃ ቤቱ ውስጥ መጣል ያለብዎት ከሰው ሆድ ውስጥ የሚወጣ ቆሻሻን እና የሽንት ቤት ሶፍትን ብቻ ነው።

- ለአንድ ጊዜ አገልግሎት ብቻ የሚውሉ መጥረጊያዎች በምርት ማሸጊያቸው ላይ አምራቾች መጸዳጃ ቤት ውስጥ ሊጥሏቸው ይችላሉ ቢሉም እንኳን ባንቧ ሊዘጉ ይችላሉ። እነዚህ ዕቃዎች ከመጸዳጃ ቤት ወረቀት የበለጠ ወፍራም ሲሆኑ፣ በቀላሉ በቧንቧዎች እና በፍሳሽ ማስወገጃዎችም ውስጥ መደፈንን በማምጣት ከፍተኛ ወጪ የሚያስወጣ የቧንቧ ጥገና ሥራ እንዲካሄድ ያደርጋሉ።
- የማብሰያ ዘይቶች እና ቅባቶች ከቧንቧዎች ጋር ተጣብቀው ባንቧው እንዲዘጋ እና ፍሳሽ እንዳይሄድ ያደርጋሉ። ቅባት ውኃ ውስጥ አይሟሟም።
- በዝርዝሩ ላይ የተጠቀሱት በርካታዎቹ እቃዎች በትክክል መሰባበር የማይችሉ ሲሆኑ፣ በቤትዎ፣ በጎዳናዎች እና በቆሻሻ ማጽጃ ፋብሪካዎችም ውስጥ ባንቧ ሊዘጉ እና ሁኔታዎችን ሊያበላሹ ይችላሉ።

### ቤትዎን እና አካባቢዎን ጤናማ አድርገው ያቆዩ

መድኃኒቶችን ወይም ኬሚካሎችን በጭራሽ በመጸዳጃ ቤት በኩል አይጣሉ

- መድኃኒቶች እና ኬሚካሎች በአግባቡ ካልተወገዱ በጅረቶች፣ ወንዞች እና ውቅያኖሶች ላይ ጉዳት ያስከትላሉ።
- መድኃኒቶች  በመጸዳጃ ቤት ወይም በማጠቢያ በኩል ወደ መጣል የለባቸውም። መድኃኒቶችን ለማስወገድ ከፈለጉ ወደ ከተማው አንዱ የመድኃኒት ማስቀመጫ ቦታዎች ሊወሰዷቸው ወይም በአካባቢዎ ያለ ፋርማሲን ሊያነጋግሩ ይገባል።
- የማይፈለጉ የቤት ማጽጃ ወይም ዲስኢንፌክታንት ምርቶች ካሉዎት ወደ ቀጣዩ የቤት ውስጥ አደገኛ ቆሻሻ ቀን ይዘዋቸው ሊመጡ ይችላሉ



የከተማ አስተዳደር
CAMBRIDGE